ትክክለኛ የእጅ አስተጣጠብ ቅደም ተከተል



የስራ ቦታ ደህንነት በኮሮናቫይረስ በሽታ (ኮቪድ-19) - ለ ሁሉም

በሃገራችን ሰዎች በኮሮና ቫይረስ መያዛቸውን ተከትሎ የቫይረሱ ስርጭት እንዳይስፋፋ እና የሁሉንም ጤና እና ደህንነት ለማረጋገጥ በድርጅት ባለቤቶች/አሰሪዎች እና ሰራተኞች ወይም ተቀጣሪዎች መደረግ ያለባቸው ጥንቃቄዎች አሉ። እነዚህንም ልብ ብሎ መተገብር ይገባል።

- በኮሮና ቫይረስ በሽታ ዙሪያ ዝግጁነት መጨመር
- በኮሮና ቫይረስ በሽታ የሰራተኞችን እውቀት እና ክህሎት በማሳደግ በስራ ገበታቸው ላይ የራሳቸውንም ሆነ የሌሎችን ጤና እና ደህንነት ለመጠበቅ እንዲችሉ ማድረግ
- በስራ ገበታ ላይ ከኮሮና ቫይረስ ጋራ በተገናኘ በሰራተኞች፥ ቀጠጣሪዎች እና ደንበኞቻቸው መካከል አድሎ እና መገለልን መከላከል።

የኮሮናቫይረስ ስርጭትን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር የሚደረገው ጥረት ስኬታማ እንዲሆን የሁሉም ሃላፊነት እንደመሆኑ መጠን ቀጣሪዎች፤ ሰራተኞች እና ደንበኞች ማንኛውንም የጤና እና የደህንነት ተግባራት ማክበር ይጠበቅባቸዋል።

ለበለጠ መረጃ
በነፃ የስልክ መስመሮች
8335 ወይም 952
ላይ ይደውሉ

የኮሮናቫይረስ በሽታ በቀላሉ የሚሰራጭ እና እስከሞት የሚያደርስ ስለሆነ መደበኛ ስራዎች እንኳን ማለትም አካባቢን፤ የስራ ቦታን ማጽዳት፤ የግል ንጽህናን መጠበቅ በተለየ ጥንቃቄ መከናወን አለባቸው። ከነዚህ ጥንቃቄዎች መሃከል

- ሰዎች በተደጋጋሚ የሚነካኳቸውን ቦታዎች እና እቃዎች ቶሎ ቶሎ ማጽዳት እና በጸረጀርም ማጽጃ ማጽዳት
- የበር እጀታዎችን፤ የሊፍት ቁልፎችን (ሰዎች የሚጫኑዋቸውን) ፤ የኤቴም ማሽን መተላለፊያዎች፤ የመፈተሻ ብረቶች፤ የእንግዳ መቀበያ ስፍራ፤ የደረጃ መደገፊያ የመሳሰሉትን በተደጋጋሚ በጸረ ጀርም ማጽጃ ማጽዳት
- ተጨማሪ እጅን የማጽጃ ቦታዎች መጨመር እና እጅን በትክክል እና በአግባቡ የማጽዳት ዘዴዎችን ሁሉም ሰራተኛ እንዲያውቅ እና እንዲተገብር ማድረግ
- ለሁሉም ሰራተኛ የሚያገለግል የንጽህና አጠባበቅ እና እጅን ከጀርም ነጻ የማድረጊያ መመሪያዎችን እና አተገባበሮችን ከጊዜው ጋር በሚሄድ መመሪያ መተካት

በቫይረሱ የመያዝ ስጋትን ለመቀነስ ሁሉም ሰው ድርሻዉን ሊወጣ ይገባል

- እጅዎን በሳሙናና በውሀ ቶሎ ቶሎ ይታጠቡ። አሊያም አልኮል ባለው የጀርም ማጽጃ በማሸት ያጽዱ

- አይንዎን፣ አፍንጫዎን እና አፍዎን በእጅዎ ከመንካት ይቆጠቡ

- ከሰው ጋር የሚደረግ ማንኛውንም ንኪኪ ያቁሙ። ለሰላምታም ቢሆን ከመጨባበጥ፣ ከመሳሳም፣ ከመተቃቀፍ ይቆጠቡ።

- ሰዎች በሚበዙባቸው ቦታዎች አይገኙ፣ በመካከላችሁ ቢያንስ 2 የአዋቂ እርምጃ ያህል ርቀት እንዲኖር ያድርጉ



- በሚያስሉ እና በሚያስነጥሱ ጊዜ አፍ እና አፍንጫዎን በሶፍት ወይም ክርንዎን በማጠፍ ይሸፍኑ፤ የተጠቀሙበትን ሶፍት ወይም ተመሳሳይ ነገር በአግባቡ ያስወግዱ